# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ
# ለንደን
# Embassy of The Federal Democratic Republic of Ethiopia
# LONDON

**ቀን፡ ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም.**

**<u>የታክስ መለያ ቁጥር /ሠርቲፊኬት/ ለማግኘት የጣት አሻራ ያልሰጣችሁ ኢትጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ</u>**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአገሪቱን የታክስ አሰባሰብ ሥርዓት ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ በአገራችን ውስጥ በግብር ከፋይነት የሚታወቅ ግለሰብ በአካል በመቅረብ የጣት አሻራቸውን በመስጠት የታክስ ሰርቲፊኬቱን መውሰድ እንዳለበት መመሪያ መውጣቱ ይታወቃል።

በዚህም መሠረት የጣት አሻራ መስጠት የሚቻልበት የጊዜ ገደብ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም. ድረስ የሚጠናቀቅ መሆኑ በመመሪያው መጠቀሱ ይታወሳል። በመሆኑም በዩናይትድ ኪንግደም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ እና የጣት አሻራቸውን በመስጠት የግብር ከፋይነት ሠርቲፊኬት በመውሰድ ላይ ይገኛሉ።

ይሁን እንጂ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ይህን ማድረግ ያልቻሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ አትዮጵያውያን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ ይቻል ዘንድ ኢትዮጵያ ውስጥ የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ያላችሁና ግብር ከፋይ የሆናችሁ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያን በስልክ ቁጥር 02078383884፣ በፋክስ ቁጥር 020758470454፣ በኢ-ሜይል info@ethioembassy.org.uk ወይም በአካል በኤምባሲያችን በመገኘት ስማችሁን፣ አድራሻችሁን፣ የስልክ /ሞባይል ወይም ላንድላይን/ ወይም የኢ-ሜይል አድራሻችሁንና ኢትዮጵያ ውስጥ ያላችሁን የንግድና ኢንቨስትመንት ዓይነት በአስቸኳይ እንድታስመዘግቡ እንጠይቃለን።

ከሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ ለንደን
Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia

17 PRINCES GATE
LONDON SW7 1PZ
www.ethioembassy.org.uk

TEL: 0207 589 7212
FAX: 0207 584 7054
e-mail:info@ethioembassy.org.uk